# እሳቱን ለኩሶ በ11ኛው ሠዓት ወደ ፓርላማ….

**ታደገ ከካዛንችስ** (sofiateshome@yahoo.com)

ከዘመናት የንጉሳዊና ወታደራዊ አምባገነን የመንግስት ሥርዓቶች ተላቀን ህዝብ ያስተዳድረኛል ብሎ ያመነበትን አካል በድምፁ ስልጣን የሚሰጥበትና እራሡን ብቸኛው የመንግስት ሥልጣን ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥበት መንገድ ተመቻችቶለታል፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት በስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ የህዝብ ሥልጣን ባለቤትነትን ያረጋገጡ ሦስት አገራዊና ክልላዊ ምርጫዎችን አሣልፈናል፡፡ እነሆ አራተኛውን ለማስተናገድ ሽር ጉድ ይዘናል፡፡

ከተደረጉት ምርጫዎች በተለየ መልኩ ምርጫ 97 የሁሉንም ትኩረት የሳበ ነበር ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡ ይህ ምርጫ በአሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪካዊ መልኩ ተካሂዷል፣ አስደናቂና አለምን ያስገረሙ ሁነቶች ተስተናግደዋል፡፡ የአገራችን ፓርቲዎችም ፍትሃዊ የአየር ሽፋን አግኝተው የምረጡኝ ዘመቻ በነፃነት አድርገዋል፡፡

በወቅቱም ከአመቱ የመጀመሪያ ወራት ጀምሮ በህዝብ የመገናኛ ብዙሃን ቀጥታ ሥርጭት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች አቋማቸውን ለህዝብ የማስተዋወቅና የምረጡኝ ቅስቀሳ ማድረግ፣ እንዲሁም ለምርጫው ጥቂት ቀናት እስኪቀሩት ድረስ የደመቀና በተለይ ደግሞ ጠንካራ ተፎካካሪዎች በነበሩት በኢህአዴግና በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ መካከል የህዝብን ቀልብ የሳበ ሁኔታ ነበር፡፡ ይህ የምርጫ ሂደት የሚያመለክተው ምን ያህል ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ አካሔድ የነበረ መሆኑን ነው፡፡

የ1997ዓ.ም. አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ከመደረጉ በፊት እንግዲህ ሂደቱ በዚህ ያበቃ አልነበረም፡፡ ድምጽ ለመስጠት ከየአቅጣጫው ተመዝግቦ በነቂስ የወጣው ህዝብ ቁጥር ታይቶ የማይታወቅ ነበር፡፡ በተቃውሞ ጐራ የተሠለፉት ፓርቲዎችም ሠላማዊ በሆነ መልኩ ያላቸውን አቋም በግልጽ ያስቀመጡበትና ሠፊ ድጋፍ

*የሚያስገኝላቸውን ነገር ሁሉ ያደረጉበት ወቅት ሆኖ አልፏል፤ በስተመጨረሻ ውጤቱ የከፋ ሆነ እንጂ፡፡*

*እናስ ወዳጆቼ አራተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ ወራቶች ቀርተውት እያለ የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን እያደረጉ ነው የሚለውን ጉዳይ ተመልክታችኋል? የዘንድሮው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ዝግጅት ከ1997ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር ምን እንድምታ አለው? ወዘተ የሚሉትን ጉዳዬች እስኪ ትንሽ ጀባ ልበላችሁ፡፡*

*የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ማየት ከጀመርን ጀምሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ በርካታ ችግሮች ሲከሠቱ ማስተዋል ብዙም አዲስ አይደለም፡፡ ሌሎችን የችግር ጊዜአት ልተወውና ከ97ቱ ምርጫ በኋላ የተፈጠረው የፓርቲዎች መፈረካከስና ለመጪው ምርጫ በቂ ዝግጅት በሚደረግበት በአሁኑ ወቅት በተለያየ መልኩ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲነታረኩ መመልከትና እከሌ ባለበት ወይም በደረሠበት ውይይት ላይ ድርስ አልልም፤ አሊያም ደግሞ እኔ መወያየት የምፈልገው ከእከሌ ፓርቲ ጋር ብቻ ነው ወዘተ... የመሳሰሉትን ማንሳት ይቻላል፡፡*

*የሚገርመው ነገር / ጉዳይ/ ግን አሁን ድረስ ችግሮቹ መፈታት አለመቻላቸው ነው፡፡ ለሠው ልጅ መቼም በአንድ ወቅት ከሠራቸው ስህተቶች ትምህርት ወስዶ ወደፊት ላቀዳቸው ሥራዎች ግብዓት ማድረግ ያዳግተዋል ብዬ አላምንም፤ ሌላ ተንኮል ወይም ክፋት ካልተመኘ በስተቀር፡፡*

*እናም በቅርብ ጊዜ በምርጫ ወቅት ሊነሱ የሚችሉ አላስፈላጊ ግጭቶችን ለማስወገድ፣ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ ምርጫ ውድድርን ለማበረታታትና የተለያዩ የመብት ጥሠትን ለመከላከል የሚያግዝ ሠነድ አውሮፓ በሚገኝ አንድ ኢንተርናሽናል ተቋም ተዘጋጅቶ ገዥውና ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲወያዩበት በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተከሠተውን ችግር ማንሳት ይቻላል፡፡*

የሁለት ግለሠቦችና የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ የሆነው መድረክ በዚህ የስነ - ምግባር ደንብ ላይ ውይይት እየተደረገ ባለበት ወቅት ድርድር አቋርጦ ወጥቷል፡፡ ይህ ፓርቲ በድርድር ወቅት ተጨማሪ ጊዜ ይሠጠኝ የሚል ጥያቄ አቅርቦ የጠየቀው ቢፈቀድለትም፣ ተጨማሪ ጣጣ ይዞ ተመለሰ፣ ‹‹ድርድር ማድረግ የምፈልገው ከገዥው ፓርቲ ጋር ብቻ ነው›› በሚል የሌሎችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሐሳብ ጠቀሜታ እንደሌለው፣ ሌሎችን አሳንሶ በመመልከት ድሮ የተጠናወተው ስሜት አንፀባርቋል። ጊዜው ግን አንዱ እንዱን የሚንቅበት ሳይሆን አንዱ ከሌላው በመማር ጉድለትን ተባብሮ ለመድፈን ጠንክሮ የሚሰራበት መሆን በመዘንጋት ነው፡፡

ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር በአንድ ቤተሠብ ውስጥ አንድ በጥባጭ ካለ ቤተሠብ ብቻ ሳይሆን ጎረቤትና አካባቢውም መረበሹ የማይቀር መሆኑን ነው። በመሆኑም ከላይ የጠቀስኳቸውን ችግሮች በአንድ መሪ ወይም ጋሪ እንዲጓዙ በሚጠመዝዙ አምባገነን ግለሠቦች የሚከሠቱ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም፡፡ አምባገነን ባህሪ ደግሞ ብቻውን ሳይሆን የሚቆመው አጠቃላይ የፓርቲውን መንፈስ መቀየሩ አይቀርም፡፡

መድረክ ሠሞኑን ባደረገው የፓርቲዎች ጥምረት አመራር መረጣ ላይ ዶ/ር መራራ ጉዲናን የመድረኩ ሊቀመንበር፣ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራውን ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር እና የምርጫ ጉዳዬች አስፈፃሚ አቶ ገብሩ አስራትን ደግሞ ተቀዳሚ ም/ሊቀመንበር እና የህዝብ ግንኙነት ሐላፊና ሌሎችንም አመራሮችን መምረጡ ይታወሳል፡፡

በጣም የገረመኝና ያስፈራኝ ነገር ቢኖር የዶ/ር መራራ ጉዲና ሊቀመንበር ሆኖ መድረኩን እንዲመሩ መመረጣቸው ነው። መጀመሪያ ደረጃ ፓርቲዎች አመራራቸውን መምረጥ የራሳቸው የውስጥ ስራ ቢሆንም የዶ/ር መራራ ጉዲና መመረጥ ግን በሃገራችን የተጀመረውን የዴሞክራሲ ሂደት የተቃና ያደርገዋል ብዬ አላምንም፡፡ ምክንያንቱም እሳቸው በተለያየ ጊዜ በራዲዮም ሆነ በህትመት ሚዲያው የሚሠጡት ቃለ ምልልስ ወይም መግለጫ የሚያስማማና ለሀገር

የሚጠቅም ሳይሆን ሁሌም ለንትርክና ብጥብጥ የሚዳርግ ከመሆኑም ባሻገር ንግግራቸው ሁሌም ፍጥጫና ተንኳሽ ሆኖ አይቸዋለሁ፡፡

ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ አማርኛ ፕሮግራም ጳጉሜ 03/2001 ዓ.ም የሠጡትን ቃለ ምልልስ ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ ዶ/ር መራራ ሲገልፁም ከምርጫ ስልጣንን አንጠብቅም ‹‹የሚሻለው መንገድ እንደ ዝምባቡዌና እንደ ኬኒያ የስልጣን መጋራት ስምምነት ነው››ነበር ያሉት፡፡ ታዲያ ይህ አይነት ቅስቀሳ ወንዝ ሊያሻግራቸው ይችላል? የሚሉትን ጥያቄዎች በደንብ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ቢኖር ለመጪው ምርጫ በቂ ዝግጅት አለማድረግ ለነዚህ ተጠቃሽ አማራጮች ቅየሳ እንደዋና ምክንየት ሊወሠድ ይችላል፡፡ ሌላው ነገር ደግሞ ገዥው ፓርቲ የአባላትን ቁጥር ስለጨመረና ስላጠናከረ በመጪው ምርጫ ልናሸንፍ አንችልም የሚል ፍራቻ ነው፡፡ አባላትን ማፍራትና ብዙ ደጋፊ ማግኘትን እንደ እርግማን ተቆጥሮ የሆነ ያልሆነውን በመቀባጠር የራስን የቤት ስራ ካለመስራት የመጣን ስንፍና በሌሎች ላይ ለማላከክ የሚደረግ ሙከራ ያስመስላል።

ምን አልባት የአመራር አመራረጡ የብሔረሠብ መልክ ለመስጠት ታስቦ ከሆነ ጥሩ መስሎ ሊታይ ይችላል፡፡ ይህ ቢታሠብም ግለሠቡ ግን ፍጥጫና ንትርክ የሚፈልጉ በመሆናቸው መጪውን ምርጫ ሠላማዊ ያደርጉታል የሚል እምነት መጣል የዋህነት ነው፡፡ በ1997ዓ.ም ምርጫ ወቅት ሌሎችን ለጥፋት አጋፍጠ በአስራ አንደኛው ሠአት ወደ ፓርላማ እገባለሁ በማለት ሲሸውድ የነበረን አካል አሁንም ድራማህን አሳየን ተብሎ ከሆነ ስህተቱ ባይደገፍ ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ ምክንያቱም በእሳት መጫወት ውጤቱ አያምርምና! ግለሰቡ ሰላማዊ ፖለቲካን ከማራመድ ይልቅ በንግግራቸው ሁሉ ዛቻ፣ ስድብና የሃይል እርምጃዎችን የሚወዱ መሆናቸውን ደጋግመን አይተናቸዋል።

ሲፈልጉ በአለም አቀፍ ታዋቂ የሆነና የብዙ አገሮችን ተሞክሮ የያዘ የምርጫ የስነ ምግባር ደንብ ሠነድ ላይ ድርድር አላደርግም የሚሉ፤ ሲፈልጉ ደግሞ ለሀገርና ለወገን ከፍተኛ ማህበራዊ ኃላፊነትን የተሸከሙ ባለሀብት ላይ በመጪው ምርጫ

ወቅት ታላቅ አጀንዳ እናደርጋቸዋለን በማለት ታጥቀው ይነሳሉ፡፡ ሲያሰኛቸው ህገ መንግስቱን ያጣጥላሉ ብቻ ከእርሳቸው ማብጠልጠል የተረፈ አንድም ነገር የለም፡፡

እንግዲህ ይህን መሠል አጀንዳ እደግድገው የተነሡ ፓርቲዎች ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ነገር ያመጣሉ ብሎ መጠበቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ መድረክ የምርጫ ቅስቀሳ በሚደረግበት በአሁኑ ጊዜ አመራሩን ሲመርጥ ፓርቲውን በሊቀመንበርነት ለአራት ወራት እንዲመሩ የተደረጉት ዶ/ር መራራ ቀጣዩን ምርጫ ሠላማዊ ሊያደርጉት ይችላሉ የሚለው ጥያቄ ይበልጥ ሁኔታዎችን አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል፡፡

የእርሳቸው መመረጥ ሆን ተብሎ ምርጫው ነፃና ሠላማዊ እንዳይሆን ተፈልጐ እንጂ እውነት ከፓርቲው አባላት ውስጥ ሀጋዊና ሠላማዊ ዝንባሌ ያላቸው ወይም በሳል አስተሣሠብና የመቻቻል ፖለቲካ የሚያራምዱ አመራሮችን አጥተው ነው ያሰኛል? ለአመፅና ለሁከት፣ ለስድብና ለንትርክ በርግጥ የተሻለ ሰው ስለሌለ የግድ ዶ/ር መራራ ጉዲናን መምረጣቸው አይፈረድባቸውም፡፡ ይህ ደግሞ ፓርቲው እራሡን እንደ እሳት እራት ወደ እሳት እየከተተ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እኛ የምንፈራው የፓርቲው እሳት እራት መሆን ብቻ ሳይሆን በአገራችን ዳግም የ97ቱን አይነት መርን ያጣ ሁኔታ እንዳይከሰት ነው።

በአሜሪካ የሽብር ጥቃት በተፈፀመበት ወቅት አሜሪካኖች ቡሽን ሲመርጡ ሽብርተኝነትን አሳደው ይይዙልናል፡ እኛም ሠላማዊ ኑሮን እንጀምራለን በማለት ሲሆን አርባ አራተኛ ፕሬዚዳንታቸው የሆኑትን ባራክ ሁሴን ኦባማን ሲመርጡ ደግሞ ጦርነትን በሠላማዊ መልኩ ሊፈቱልን ይችላሉ፣ በወቅቱ የገጠማቸውን የኢኮኖሚ ቀውስ ይታደጉናል በሚል እሳቤ መሆኑን ማየት ይጠቅማል፡፡ ስለዚህ መድረኮችን ህዝቡ ሊመርጣቸው የሚችለው በአጠቃላይ የፓርቲዉን መንፈስ በመረዳት እንጂ ሌላ መመዘኛ ኖሮት አይደለም፡፡ ከዚህ የምንረዳው መድረኮች ንትርክ የሚወዱትንና ተናዳፊ የሆኑትን ዶ/ር መራራን የመረጡት ሰላማዊ ትግልን ካለመፈለግና ነውጥና ብጥብጥን ፍለጋ ይመስለኛል።

አሁን ከመድረክ አመራሮች አባባል በቀላሉ መረዳት እንደምንችለው ለዚች አገር ሠላም ቅንጣት ያህል የማይጨነቁ መሆናቸውን ነው፡፡ አላማቸው አድርገው የተነሡት በምንም መልኩ ይሁን በትረ ስልጣኑን የሚያገኙበትን መንገድ ብቻ መቀየስን ነው። በሰላማዊ መንገድ ስልጣን ለመያዝ ደግሞ ከኢህአዴግ ጋር ተወዳድሮ ማሸነፍ እንደማይችሉ ከወዲሁ በመረዳት ስልጣን የሚይዙበትን መንገድ መቀየሡን ይፋ አድርገዋል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ የዝምባቡዌንና የኬንያን ፈለግ ተከትለን የፈለግነውን ያህል ህዝብ ይለቅ፣ በሺዎች የሚቆጠሩትም ይሠደዱ ስልጣን መጋራት አለብን የሚለው የቅስቀሳ ዘመቻ አዋጭነት የሌለው ስለሆነ ከወዲሁ አንድ ነገር ልንለው ይገባል፡፡ ሁሌም ለሠላማዊ ህዝብ ትንሽም ክብር ባለመስጠትና ለራስ ጥቅም ታጥቆ በመነሳት ፖለቲካ ውስጥ መግባት አደገኛ አካሔድ ስለሆነ መስተካከል ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ቀደም እንደተደረገው ሃገርንና ህዝብን ለጥፋት ዳርጐ በ11ኛው ሠዓት ወደ ፓርላማ እገባለው የሚባል ውዳሴ ዛሬም እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊቸረው ይገባል እላለሁ፡፡ ቸር እንሠንብት